# ተከድኖ ይብሰል!

የርሱ ኣመጣጡ
ደረጃ ኣወጣጡ
ጠፍቶ መላቅጡ
ወድቆ መላላጡ
ነገሩ ሲዘረዘር
ለነገ ብየ ነበር



እንዲህ ቸኩላችሁ
ዛሬ ከመጣችሁ
ምን ሳልደብቃችሁ
ሁሉን ልንገራችሁ
ነገሩስ ነገር ነበር
ኋላስ ወድቆ ቢሰበር



በጨለማ ውድቅት
ኣስፈሪው ሰዓት
በጥንት ነብያት
ተነገሮ ትንግርት
ፍጹም የማይሆን ነገር
የሚሆን መስሎኝ ነበር



ልበ-ቢስ ከርፋፋ
ታኘኮ እስኪተፋ
ከጭንና ታፋ
የቱ ነው ቀልጣፋ
እርሷ ባመጣችው
ወዴት ደበቀችው

እንዲያው ለሰው ይምሰል
የሰው ልብን ማቁሰል
ድስቱ ሳይማሰል
ተከድኖ ይብሰል-ሰል
ኣትንኩት ነገሩን
ኣታንሱት ምስጢሩን



ማንም ኣላወቀ
ይኸ ኣቶ ፈለቀ
ልብሱን ኣወለቀ
ከወንዝ ተደበቀ
ኣንድ ሳይንገራገር
ለሰው ሳይናገር



ወይ የሰው ልጅ ዕጣ
ምስጢሩ ሳይወጣ
ያየው እንዲቀጣ
ይውረድ ከሰንቃጣ
ምንም ሳትገደድ
ኣብራ እንትሰደድ



ማንንም ኣይፈራ
ግን ጉዱ እስኪጣራ
ሰውም ኣይጠራ
ምን ተበሎ ይወራ
እርሷ ኣብራ መሄዷ
በውድ በፈቃዷ



ከሳር ከቅጠሉ
ቁንጫ ቅማሉ
ከዶሮ ዕንቁላሉ
ይበልጣል ኣስኳሉ
የምስጢሩ ቁምነገር
ለማንም ኣይነገር





ትርምሱ ይቆማል
ትንቢቱ ይፈጸማል
ሰው ሁሉ ይገረማል
ፈርማውም ይፈረማል
ትንቢቱ ሲመረመር
ከሁሉም እንዲጣመር




ገ/ኢ. ጐርፉ።